*ኢዮሃ አበባዬ !*

*ኢዮሃ አበባዬ*
*መስከረም ጠባዬ*
*አይኔ ተቃጠለ ነደደ በንባዬ*

*የህጻናቱ ድምጽ ባህርን አቋርጦ*
*እንደ ፈረስ ጋልቦ እንደ ፈረስ ሮጦ*

*በአደይ አበባው*
*ሜዳ በተረጨው*

*በሱ ተቆስቁሶ ያለፈው ትዝ አለኝ*
*እንደ ጫማ ጠጠር ልቤን ቆረቆረኝ*

*አስታውስሻለሁ በነፍሴ እሪ እያልኩኝ*
*ከልቤ ጨምቄ ደም እያለቀስኩኝ*

*ከትዝታ በቀር በአካል ላላይሽ*
*ቃል ኪዳን ነው ያለኝ ቃል ኪዳን ነው ያለሽ*

*ኢዮሃ አበባዬ*
*መስከረም ጠባዬ*
*አይኔ ተቃጠለ ነደደ በንባዬ*

*እኔም ልጅ ነኝና ካብራክሽ የወጣሁ*
*ከድፍርሱ ምንጭሽ ከጡትሽ የጠጣሁ*

*በደረቀው ወንዝሽ በደም የተጠመቅሁ*
*በተራራሽ ሮጬ በትከሻሽ ያደርሁ*

*በቀይ ነጩ ሽብር በጣር ውስጥ ያዘልሽኝ*
*ከወረቀት በታች ጠቅልለሽ ያቀፍሽኝ*

*እራቁት ገላዬን በሆድሽ ያረገዝሽው*
*የጥይቱን ዋጋ እዳ የከፈልሽው*
*በድኔ እንዲቀበር ነጻ የለቀቅሽው*

*ነውሬን የሸፈንሽው*
*ራቁት አፍረቴን ሚስጥሬን የያዝሽው*

*መልካም ይሁን ላንቺ*
*ዘላለም አትሙቺ*

*አብቢ እንደገና እንደ አደይ አበባ*
*ፈገግታሽ ይመለስ ይድረቅ ያይንሽ እንባ*

*እድሜ ጸጋ ሆኖሽ እንደገና ፍኪ*
*ለህያው ለሙታን ታሪኩን ተርኪ*

*ኢዮሃ አበባዬ*
*መስከረም ጠባዬ*
*አይኔ ተቃጠለ ነደደ በንባዬ*

***ለታደሰ አበበ** (1961-1980 **አ ም**)*
*Zewdu Sahlu*
*November 2008*

***Back to Meskot***

---

***The views reflected in the above poem/article are solely of the author and are not necessarily shared by*** *Meskot****. You may contact Zewdu Sahlu for comments at*** *zewdu_michael@yahoo.com*